# ከኣይውሉ ውዬ





ኣምላኬ፣ ለዚህ ታቆየኝ?
ሳይቸግር - ጤፍ ብድር...
        ከኣይውሉ ውዬ!
ወንዙን ተሻግሬ - ባሮ፣
ላይ ታች ብዬ - ኣጋሮ
ልጠይቀው ስሄድ - ታስሮ
ተልጦ፣ ተመላልጦ...
ላስፈታው ስሄድ - ተሸጦ
        በኣሞሌ ተለውጦ
        ተገርፎ፣ ተቀጥቅጦ፣
        ጭንቅላቱ ተፈጥፍጦ...
ጌታዬ፣ ይህን ታሳየኝ?
ብድር - ውሎ፣ ኣያድር...
        ጉዴ፣ ወይ ዕዳዬ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።